# “ለእግዚአብሔር ምስጋና ይሁን”

የምንባብ ክፍል፤ማቴ.6፡9-10

“በሰማያት የምትኖር አባታችን ሆይ ስምህ ይቀደስ መንግሥትህ ትምጣ፤ ፈቃድህ በሰማይ እንደ ሆነች እንዲሁ በምድር ትሁን”

*መሰረታዊ የጸሎት ካርታ በሆነዉና በተለምዶ “የአባታችን ሆይ ጸሎት” እየተባለ በሚጠራዉ የክርስቶስ የጸሎት ትምህርት አስቀድሞ የተቀመጠዉ ሀረግ “ስምህ ይቀደስ” የሚል ሲሆን ይህም እግዚአብሄርን ማወደስ እንደሆነ ልብ እንላለን። እግዚአብሔር በራሱ ሙሉና ያለማንም ድጋፍ ከፍጥረት ዉጭ ጸንቶ የሚኖር አምላክ ሆኖ እያለ ከአማኞች ልጆቹ ግን ሙሉ አክብሮትና ምስጋናን፣ዉዳሴን ይፈልጋል። ይህ ሲባል ግን እኛ በማይገባን መልኩ የሆነ የጎደለዉ ነገር ኖሮት ባዶነቱን በእኛ ምስጋና ሊሞላ አስቦ አይደለም። እርሱ ሁሉን አዋቂ፣በተመሳሳይ ሰዓት በሁሉ ስፍራ የሚገኝ ፣ሁሉን የሚችል እንዲሁም በዘመናት መካከል የማይለወጥ አምላክ ነዉ አሜን። ስለዚህ ለማንነቱና ለክብሩ ምስጋና ዉዳሴ ሊቀርብለት ይገባል። ደፋና ቀና እያልን ብናመሰግነዉ የሚቀነስብን ክብር አለመኖሩ ብቻ ሳይሆን እንዲያዉም ባዎንታዊ መልኩ እየታነፅንና እየተረጋጋን እሱን ወደመምሰል የምናድግበት ፍቱን መንገድ ነዉ።*

*ሌላዉ ደግሞ እርሱ ላደረገልን ብዙ ዉለታ ሙሉ አፃፋ ይሆናል ባይባልም የምስጋና ምላሽ እንድንሰጥ የእግዚአብሄር ቃል በቀጥታ የሚያዘን መሆኑ ነዉ። ቃሉ አስፈላጊነቱን አጉልቶ ባሳየን ጎዳና ሁሉ ልንለማማደዉ የሚገባ የዕለት ከዕለት የሕይወታችን ዘይቤ መሆን የሚገባዉ ጉዳይ ነዉ።*

*“ምድር ሁሉ፥ ለእግዚአብሔር እልል በሉ በደስታም ለእግዚአብሔር ተገዙ፥ በሐሤትም ወደ ፊቱ ግቡ እግዚአብሔር እርሱ አምላክ እንደ ሆነ እወቁ፤ እርሱ ሠራን እኛም አይደለንም፤ እኛስ ሕዝቡ የማሰማርያውም በጎች ነን ወደ ደጆቹ በመገዛት፥ ወደ አደባባዮቹም በምስጋና ግቡ፤ አመስግኑት፥ ስሙንም ባርኩ እግዚአብሔር ቸር፥ ምሕረቱም ለዘላለም፥ እውነቱም ለልጅ ልጅ ነውና” መዝ.100፣1-5*

*ዉዳሴና ምስጋናን ለቅዱሱ አምላክ በምናቀርብ ጊዜ ማድረግ የሚገቡን ጥቂት ዝርዝር ሀሳቦችን ከዚህ ቀጥለን ለማስጨበጥ እንሞክራለን፡-*

## *1. እርሱን ማሰብ*

*በማመስገናችን ይደረግልን ይሆናል ወይም አንዳች ሽክም ይራገፍልኝ ይሆናል የሚለዉን የግል ትኩረት ትተን እርሱን ብቻ የምናስብበት ጊዜ ሊኖረን አስፈላጊ ነዉ ይህም ማለት በሐሳብ፣በቃል እና በድርጊት ሁሉ ሳይቀር የምናስተጋባዉ የሕይወታችን ማዕከል እንዲሆን ማድረግ ነዉ የምናስበዉን ስንናገረዉ የምንናገረዉን በተገለጠ ድርጊት ስንተገብረዉ አክብሮታችን ትኩረት ያለዉ እየሆነ ይሄዳል ስለ እግዚአብሄር ክብር የተጠቀሱ ክፍሎችን በቃል አጥንቶ እንደተፃፈዉ እንዲሁ ነህ ! እያልን ብናከብረዉ ከእዉነት ያልራቀ ስሜትም ብቻ የማይነዳዉ ሚዛናዊ የምስጋና መስዋዕት አቅራቢ ያደርገናል*

## *2. በሕይወታችን እየተሰራ ያለዉ ስራ በእግዚአብሄር እንደሆነ እዉቅና መስጠት*

*እኛ የሰዉ ልጆች በተፈጥሮአችን አንድን ነገር ለማድረግ ምክንያቱ ይህ ነዉ የምንልበት መንጠልጠያ እንፈልጋለን ስለዚህ ጌታ በሕይወታች ያደረጋቸዉን ብዙና ዝርዝር ጉዳዮች ቁጭ ብለን መቁጠርና የምስጋና ምላሽ መስጠት ይኖርብናል ለመሆኑ እግዚአብሄር በሕይወቴ የሰራዉ የበረከት ስራ አለ? እስኪ አንድ አፍታ ቆም እንበልና ለመሆኑ ጌታ ለእኔ ምን አድርጎልኛል ብለን ራሳችንን እንጠይቅ! እስኪ ዙሪያችንን እንመልከት ቤተሰቦቻችንን፣ ጓደኞቻችንን፣ጤንነታችንን፣ስራችንን፣የተሰጠን ን ልዩ የፈጠራ ችሎታ፣ ትምህርት፣ ያፈራነዉ ንብረት፣ ከተማችንን፣ ሀገራችንን እንመልከት በዉኑ በዚህ ሁሉ የማመስገኛ ምክንያት አጥተን ይሆን ይሆንን? እንዳጋጣሚ የተደረገ አንዳች ነገር በአማኝ ሕይወት እንደሌለ ልናዉቅ ይገባል። አሁንስ የጌታ እጅ ይህን ሁሉ በሕይወታችን እንደሰራች ገባን! ከስጦታዎች ሁሉ የሚበልጥ የሕይወት ስጦታ የሆነዉ ልጁ ኢየሱስ ክርስቶስ ሊካድ የማይችል የምስጋና ምክንያት ነዉ ቆጥረን የማንጨርሰዉ ብዙ ምስጋና በዉስጣችን ስላለ ቶሎ ቶሎ ብለን በፊቱ ማራገፍ ይገባናል*

## *3. በጸሎታችን ጊዜ ሁሉ ለእግዚአብሔር የሚቀርብ ምስጋናን ማስቀደም ይገባናል*

በግልም ይሁን በማህበር የጸሎት ጊዜ ከልመና ይልቅ ምስጋናችንን ማብዛት ለጥያቄአችን

የሚሆንን መልስ ያፋጥናል እንጅ የልመና ጊዜአችንን አያባክንብንም ሐዋርያዉ ጳዉሎስ ለፊልጵስዩስ አማኞች ሲፅፍ ፀሎትና ልመና እጅና ጓንት መሆናቸዉን የሚያስረግጥ ሐሳብ ፅፏል *"በነገር ሁሉ በጸሎትና በምልጃ ከምስጋና ጋር በእግዚአብሔር ዘንድ ልመናችሁን አስታውቁ እንጂ በአንዳች አትጨነቁ"* **ፊልጵ.4፡6**

በብዙ ልመና ብዛት ልናገኘዉ ያልቻልነዉን ጥያቄ የምናስመልስበት አቋራጭ መንገድ ጌታን ማምለክና ማመስገን ነዉ።ትግል በበዛበት የሕይወታችን ገጠመኝ ዉስጥ ዘና ያለ ስሜት የሚያመጣ ማጣፊጫችን ለጌታ የምናቀርበዉ ምስጋና ነዉ

### *4.ከልዩ ልዩ ስህተቶቻችን ንስሃ መግባት።*

የተገለጠም ይሁን የማይገባን ስዉር የሕይወት ስህተት ቢኖር በታማኝነት እንናዘዝለታለን ከንስሃችንም ቀጥሎ በእርግጠኝነት ወደ ልባችን የሚፈሰዉ የእግዚአብሄር ሰላም ነዉ እኛም ከዚህ እስራት ለፈታን ጌታ ምስጋናችንን ማፍሰስ እንጀምራለን ስለዚህ ንስሃ አንዱ የምስጋና ምንጭ ሲሆን እየተመለከትን ነዉ። ከሃጢያት ንስሃ መግባት ሲባል ጨፍጋጋ የሆነ ጎኑ ብቻ እየታየን ከተናዘዝንም በሁዋላ እንኳ ባልተፈታና ነፃነት በማይሰማዉ ሁኔታ የምንመላለሰዉ ይቅር መባላችንን በእምነት ተቀብለን ማመስገን ስለማንጀምር ነዉ።
*"በኃጢአታችን ብንናዘዝ ኃጢአታችንን ይቅር ሊለን ከዓመፃም ሁሉ ሊያነጻን የታመነና ጻድቅ ነው"* **1ዮሐ.1፤9**

### *5. በገጠመን ታላቅ መከራ ዉስጥ ሆነን እንኳ ብናመሰግን እስራታችን ይፈታል።*

ምስጋና የሚሰዋና ተፈቶ የሚያመልክ ሰዉ ሁሉ ጥያቄዉ የተመለሰለት ሞልቶ የተረፈዉ ነዉ ብለን የምናስብ ከሆነ ትልቅ ስህተት እንሰራለን በሌላዉ መልክ ደግሞ ነገር ሲሞላልን ብቻ በጌታ ፊት ሽርጉድ የምንል ከሆነ የተሳሳተ መልዕክት የምናስተላልፍ እንሆናለን።እዉነት እንደገባቸዉ አማኞች በየትኛዉም ሁኔታችን ዉስጥ ሆነን እርሱን እናመልከዋለን የእኛ እና የጌታ ግንኙነት የአባትና የልጅ እንጅ የመፅዋችና የተመፅዋች አይደለም

*"ሕዝቡም አብረው ተነሡባቸው፥ ገዢዎቹም ልብሳቸውን ገፈው በበትር ይመቱአቸው ዘንድ አዘዙ በብዙም ከደበደቡአቸው በኋላ ወደ ወኅኒ ጣሉአቸው፥ የወኅኒውንም ጠባቂ ተጠንቅቆ እንዲጠብቃቸው አዘዙት እርሱም የዚህን ዓይነት ትእዛዝ ተቀብሎ ወደ ውስጠኛው ወኅኒ ጣላቸው፥ እግራቸውንም በግንድ አጣብቆ ጠረቃቸው በመንፈቀ ሌሊት ግን ጳውሎስና ሲላስ እየጸለዩ እግዚአብሔርን በዜማ ያመሰግኑ ነበር፥ እስረኞቹም ያደምጡአቸው ነበር ድንገትም የወኅኒው መሠረት እስኪናወጥ ድረስ ታላቅ የምድር መንቀጥቀጥ ሆነ፤ በዚያን ጊዜም ደጆቹ ሁሉ ተከፈቱ የሁሉም እስራት ተፈታ"* ***የሐዋ.16፤22-26***

የያዝነዉ አዲስ ዓመት 2012 በሁሉ ነገሮቻችን ጌታን ማመስገን የምንለማመድበት ሲሆን በልመናዎቻችን ብዛት ሳይሆን በምስጋና መስዋዕታችን ድል የምናገኝበት እንዲሁም አባታችን የሆነዉን አምላካችንን እግዚአብሔርን የምናከብርበት ዓመት ነዉ።

*"ሁልጊዜ ደስ ይበላችሁ ሳታቋርጡ ጸልዩ፤ በሁሉ አመስግኑ፤ ይህ የእግዚአብሔር ፈቃድ በክርስቶስ ኢየሱስ ወደ እናንተ ነውና"* ***1ተሰሎ.5፤16-18***

**የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤ/ክ በካልጋሪ**
**1705 Westmount Rd NW,**
**T2N 3M4, Calgary, Alberta Canada**
**(403) 209-0914**

## Our services:

**Thursday:**
**Weekly Prayer Time:**
**6:00 pm - 8:00 pm**

**Sunday:**
**Prayer Time**
**3:00 pm - 3:30 pm**
**Worship and Sermon:**
**3:30 pm - 5:30 pm**
**Children Sunday school:**
**4:30 pm - 5:30 pm**
**Fellowship:**
**5:30 pm - 6:30 pm**

**Cell Group:**
**Seven (7) places in the City - Different days of the week**